




# በጉራፈርዳ ታጣቂዎች ጥቃት ከጀመሩበት ጊዜ አንስቶ እስካሁን ድረስ በጠቅላላው180 ያህል ዜጎች ህይወታቸውን አጥተዋል

By **አዲስ ማለዳ** - 31/05/2021

492 0

በቤንች ሸኮ ዞን በጉራፈርዳ ወረዳ ታጣቂዎች በፈጸሙት ጥቃት የአካባቢው እና የፌድራል የጸጥታ አባላትን ጨምሮ 180 ያህል ዜጎች ህይወታቸው አጥተዋል ተባለ፡፡ የቤንች ሸኮ ዞን ዋና አስተዳዳሪ ፍቅሬ አማን ከንጹሀን ዜጎች በተጨማሪም 28 የጸጥታ አካላት የህይወት መስዋዕትነት የከፈሉ ሲሆን፣ ከ29 በላይ ደግሞ ለከፍተኛ የአካል ጉዳት ተዳርገዋል ማለታቸውን ኢትዮ ኤፍ ኤም ዘግቧል፡፡

21 ሺሕ 938 የአካባቢው ነዋሪዎች ጥቃት ሊሰነዘርብን ይችላል በማለት ቤት ንብረታቸውን ጥለው መሰደዳቸው፣ እንዲሁም በጉራፈርዳ እና በደቡብ ቤንች ወረዳዎች ከ732 በላይ የቆርቆሮና የሳር ቤቶች ሙሉ በሙሉ መውደማቸው ተነግሯል፡፡

በአካባቢው የንግድ ፣የእርሻና ሌሎችም ማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች ለከፍተኛ ችግር መዳረጋቸው እንዲሁም የሕብረተሰቡ ማኅበራዊ መስተጋብርም ችግር ውስጥ መውደቁ ተገልጿል፡፡

ለሕብረተሰቡ ስጋት የሆኑት ታጣቂዎች በየጫካውና በሕብረተሰቡ መካከል ሆነው የተለያዩ ስልቶችን በመቀያየር እየተጠቀሙ አሁንም በጸጥታ ኃይሉና በንጹሀን ዜጎች ላይ አሰቃቂ ግድያና ዘረፋ እየፈጸሙ መሆኑ ተመላክቷል፡፡

---

ቅጽ 3 ቁጥር 134 ግንቦት 21 2013

---

**ተጨማሪ ጽሑፎች:**

- አካል ጉዳተኞችና የፊልም ሥራ
- የከተሞች መስፋት ያፈናቀላቸው አርሶ አደሮች ካሣ - መልሶ ማቋቋም - ስጋት
- የሆነው የአፋሮች ሕይወት

---

Like 0

Previous article
የባቡር አገልግሎቱ ዛሬ ጠዋት በመኪና አደጋ ተቋርጧል

Next article
ክፍት የሥራ ማስታወቂያ 26/09/2013

**አዲስ ማለዳ**
*http://addismaleda.com*

## መልስ አስቀምጡ

አስተያየት:

ስም:*

Email:*

ድህረገፅ:

☐ በሚቀጥለው ጊዜ አስተያየት ስሰጥ ስሜን፣ ኢሜል እና ድር ጣቢያዬን በዚህ አሳሽ ውስጥ አስቀምጥ

አስተያየት ይስጡ

## ስለ እኛ

አዲስ ማለዳ ወቅታዊ የአገራችንን ጉዳዮች በስፋትና በጥልቀት የምትተነትን፣ እንዲሁም የተረጋገጡና የትም ያልተሰሙ ዜናዎች የሚቀርቡባት የብዙኃን መገናኛ ናት፡፡ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሚዲያ ባለስልጣን በመዝገብ ቁጥር 241/2010 ተመዝግባለች፡፡

ያግኙን: info@addismaleda.com

## ይከታተሉን

© Addis Maleda 2023 a CHAMPiON Communications Publication